District of Columbia
Office of the State Superintendent of Education

# የርቀት ትምህርት ግብአት መመርያ ለቤተሰቦች

## የማስተማር እና የመማር ክፍፍል

ማርች 2020

# የዚህ የግብአት መመርያ አላማ ምንድንነው?

የዚህ መመርያ አላማ ለቤተሰቦች የርቀት ትምህርትን የሚደግፉ ግብአቶች ማቅረብ ነው። ቤተሰቦች የተማሪ(ዎች) የርቀት ትምህርትን ለመደገፍ የትምህርት ቤቶች ጋር አጋሮች ናቸው።

እያንዳንዱ ክፍል የሚያቀርበው፣

- ቁልፍ ጥያቄዎች
- እያንዳንዱን ጥያቄ ለመፍታት የሚያስችል ግብአቶች፣ እና
- ግብአቶቹን ተግባር ላይ እንዴት ማዋል እንደሚቻል መመርያ።

ይህ የተሟላ ዝርዝር ሆኖ የሚያገልግል አይደለም፣ ነገር ግን ለተማሪዎች አነስተኛ ቴክኖሎጂ እና ከፍተኛ ቴክኖሎጂ ድጋፎችን እንዴት መስጠት እንደሚቻል ከመምርያ ጋር አጋዥ የሆኑ ግብአቶችን ለመስጠት የሚያገልግል ነው።

# ቤተሰቦች የተማሪዎቻቸውን የርቀት ትምህርት እንዴት መደገፍ ይቻላሉ?

| የርቀት ትምህርት ሞዴል | የመመርያ ጥያቄዎች | ተገቢ የሆኑ ግብአቶች | እነዚህን ግብአቶች መጠቀም የሚቻልባቸው መንገዶች |
|---|---|---|---|
| **የቤት ውስጥ ልማዶች፣** ጤናማ የሆኑ የእለት ተለት ተግባሮች ተማሪዎች ወደ የርቀት ትምህርት እንዲሸጋገሩ ሊረዳ ይችላል፣ እና ቤተሰቦች እነዚህን የእለትተለት ተግባሮችን በማዘጋጀት እና በመጠበቅ ተማሪዎቻቸውን ሊረዱ ይችላሉ። | **ልጄን ለርቀት ትምህርት እንዴት ማዘጋጀት እችላለሁ?** | **የጊዜ ሰሌዳ ያዘጋጁ።** | አብዛኛው ልጆች በትምርህት ቤት ቀን የጊዜ ሰሌዳ ለምደዋል፣ ስለዚህ ተመሳሳይ አይነት ነገር በቤት ውስጥ መፍጠር ወደተለየ አይነት የትምህርት አካባቢ እንዲሸጋገሩ ሊረዳ ይችላል። |
| | | **የእረፍት ጊዜዎችን ያዘጋጁ እና የአካል እንቅስቃሴዎችን ያቅርቡ።** | ባህላዊ የትምህርት ፕሮግራሞች የተወሰነ አይነት የእረፍት ወይም ደግሞ የቤት ውጪ ጊዜ አላቸው፣ ስለዚህ በቤት ውስጥ ሆኖ የሚሰራም ከዚህ ሊለይ አይገባም። ከቤት ውጪ ጊዜ እና ንጹህ አየር ትልቅ የአካል እና የአእምሮ የጤና ጥቅሞች አሉት ። |
| | | **የእደጥበብ ይኑሮት።** | አርት የትምህርት አስፈላጊ ክፍል ነው እና ቤት ውስጥ ከልጆችዎ ጋር መስራትም ለወላጆች ለአርት የፈጠራ እድል ይፈጥራል። |
| | | **የእንቅልፍ ጊዜን ያክብሩ።** | ተለቅ ላሉ ልጆችዎ በየምሽቱ አምሽተው መተኛት እና አርፍደው መነሳት ሊያጓጓቸው የሚችል ቢሆንም፣ ጤናማ የእንቅልፍ ጊዜን መቀየር ለአካል እና የአእምሮ ጤናቸው ጠቃሚ አይደለም። |

# ብዙ ቋንቋ የሚናገሩ ቤተሰቦች የልጆቻቸውን የርቀት ትምህርት እንዴት መደገፍ ይችላሉ?

| የርቀት ትምህርት ሞዴል | የመመርያ ጥያቄዎች | ተገቢ የሆኑ ግብአቶች | እነዚህን ግብአቶች መጠቀም የሚቻልባቸው መንገዶች |
|---|---|---|---|
| **ባለብዙ ቋንቋ የቤተሰብ ድጋፎች፣**<br>ቤተሰቦች የልጆቻቸውን የርቀት ትምህርት ለመደገፍ የስነቋንቋ እና ባህላዊ እሴቶቻቸውን መጠቀም ይችላሉ። | **እኔ እንግሊዘኛ መናገር የማልችል ከሆነ ልጄ በርቀት ትምህርት ምን እንደሚሰራ፣ እንደሚማር፣ እና እንደሚለማመድ እንዴት ላውቅ እችላለሁ?** | **ልጅዎ ቤት ውስጥ በሚቆይበት ጊዜ የትምህርት ቤቱን የማስተማር እቅዳቸው ምን እንደሆነ ለመረዳት ፣እና የሚያስፈልገውን የቴክኖሎጂ ሁኔታ ለማወቅ ከትምህርት ቤቱ ጋር ግንኙነት ይኑሮት።** | የኮንፈረንስ ስነስርአቶችን፣ ቀኖችን፣ እና ጊዜዎችን በተመለከተ መረጃ ለማግኘት የልጅዎን አስተማሪ ወይም ትምህርት ቤት ጋር ይደውሉ።<br><br>የአስተማሪውን ኢሜይል ወይም ደግሞ ያለውን ሌላ የመገናኛ ቻነል (መንገድን) ማስቀመጥዎን እርግጠኛ ይሁኑ። |
| | **በርቀት ትምህርት ጊዜ ልጆቹ ስሜታቸውን መግለጽ እንዲችሉ እንዴት ልረዳቸው እችላለሁ?** | **ለልጅዎ ጆርናል ወይም ደግሞ ማስታወሻ ደብተር ይስጡ። በጆርናል ላይ መጻፍ፣ ስኬች ማድረግ፣ ወይም መሳል ተማሪዎች በዚህ እርግጠኛ ባልሆነ ጊዜ ውስጥ ስሜቶቻቸውን እንዲያደምጡ ይረዳቸዋል።** | ስለወረርሽኙ እያንዳንዱ ሰው ምን እየተሰማው እና እንዴት እየተቋቋመው መሆኑን እንደቤተሰብ ለማውራት ጊዜ መመደብ ትችላላቹ። |
| | **እኔ እንግሊዘኛ መናገር የማልችል ከሆነ የልጄን ስራዎች እንዴት መከታተል እችላለሁ?** | **አብዛኛው የኦንላይን ክፍለጊዜዎች ምናባዊ ስብሰባ አይደሉም። በተማሪው የራሱ እርምጃ የሚከናወኑ የቤት ስራዎች፣ የውይይት ሰሌዳዎች፣ መድረኮች፣ እና ፕሮጀክቶች አሉ። ልጅዎ ከአስተማሪዎ ጋር በተመሳሳይ ክፍል ውስጥ አይደሉም። ለመርዳት እርስዎ ከልጅዎ ጋር በተመሳሳይ ክፍል ወይም እንግሊዘኛ መናገር እንዳለብዎ አያስቡ።** | እርስዎ የታዘዘውን የትምህርት ይዘት እና/ወይም የትምህርት ስራዎች ላይ ለማውራት ጊዜ መመደብ ይችላሉ።<br><br>ልጅዎ የወደዱትን የእሱን/የሷን ተግባር ምን እንደሆነ ፣ የትኛው ተግባር ለማከናወን በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ፣ እና ምክንያቱን ይጠይቁ፣ |
| | **በርቀት ትምህርት ጊዜ ልጄን ለመርዳት የመማሪያ ቋንቋውን መናገር አለብኝ?** | **በርቀት ትምህርት ጊዜ ልጅዎን ለመርዳት የመማርያ ቋንቋውን መናገር አያስፈልግዎትም።**<br><br>**እርስዎ ሀሳቦችዎን ለመግለጽ ወይም ደግሞ መመርያዎን ለመስጠት በጣም** | እርስዎ ኤክስፐርት (ባለሞያ) መሆን አያስፈልግዎትም! ሊያደርጓቸው ከሚችሏቸው በጣም ደጋፊ ነገሮች ውስጥ አንዱ ልጅዎ በምርምሮቹ እና ሀሳቡ ላይ የእነሱ አጋር መሆን ነው። በሚያከናውኑበት ጊዜ የሚያስቡትን ነገር |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | **የሚመችዎትን ቋንቋ ሁሉጊዜ መጠቀም ይችላሉ።** | ጮክ ብለው ይናገሩ ወይም ይግለጹ፣ ማብሰል፣ አንድን ነገር መጠገን፣ የቤት ውስጥ እንስሳቶችን መንከባከብ፣ ወይም ሌላ የቤት ውስጥ ስራ መስራትን ሊሆን ይችላል። ጥያቄዎችን ይጠይቁ፣ መልሱን የማያውቁት ቢሆንም እንኳን! |

# በርቀት ትምህርት ጊዜ የእንግሊዘኛ ተማሪዎችን ሊረዱ የሚችሉ ግብአቶች ምንድን ናቸው?

| የርቀት ትምህርት ሞዴል | የመመርያ ጥያቄዎች | ተገቢ የሆኑ ግብአቶች | እነዚህን ግብአቶች መጠቀም የሚቻልባቸው መንገዶች |
|---|---|---|---|
| **Supporting Families of English Learners (ELs) (የእንግሊዘኛ ተማሪዎች የሆኑ ቤተሰቦችን መደገፍ) (ELs)** | **ወላጆች በልጃቸው ላይ የቤት ውስጥ ቋንቋ እድገትን እንዴት ማበረታታት ይችላሉ?** | የአራት ሳምንት ካላንደር | ማውረድ የሚቻል ካላንደር ቤተሰቦች የቋንቋ ትምህርትን በእለት ተለት ተግባሮቻቸው ላይ እንዲያካትቱት ያስችላል፣ በእንግሊዘኛ፣ ስፓኒሽ፣ ፖርቹጊዝ፣ ሶማሊኛ፣ አረብኛ፣ ቻይኒዝ፣ ፈረንሳይኛ፣ ኡርዱ፣ እና ቬትናሚዝ (ከመዋእለህጻናት- 8) |
| | | የክፍል ደረጃን -መሰረት ያደረገ መመርያዎች | እነዚህ መመርያዎች ወላጆች ተማሪያቸውን በትምህርት ቤት ስራ ቤት ውስጥ እንዲያጉዟቸው ይረዳቸዋል፣ ከ National PTA በእንግሊዘኛ እና በስፓኒሽ የሚገኙ። |
| | **ቤተሰቦች ስለ COVID-19 ወረርሽኝ እና የራሳቸውን እና የቤተሰቦቻቸውን ደህንነት እንዴት መጠበቅ እንደሚችሉ የሚማሩባቸው ግብአቶች ምንድን ናቸው?** | **Center for Disease Control (CDC) Coronavirus Resource Center and Fact Sheets (የበሽታ ቁጥጥር ማእከል የኮሮናቫይረስ ግብአት ማእከል እና የፍሬነገሮች ገጾች) በ** እንግሊዘኛ፣ ቻይኒዝ፣ ስፓኒሽ | የ CDC ገጽ ስለኮሮናቫይረስ ምልክቶች፣ ማን ተጋላጭ መሆኑን፣ በሽታውን እንዴት መከላከል እንደሚቻል፣ እና ከታመሙ ምን ማድረግ እንደሚገባዎ አጠቃላይ መግለጫ ይሰጣል። |
| | | Colorin Colorado (ከለሪን ኮሎራዶ) | COVID-19 የፍሬነገር ገጾች በበርካታ ቋንቋ**ዎች** |
| | | ማይክሮሶፍት አስተርጓሚ | የCOVID-19 ግብአቶችን የቋንቋ ተደራሽነት ለማገዝ ላይቭ የጽሁፍ (የምስል) መግለጫ እና ትርጉም። |
| | **በ COVID-19 ምክንያት ቤተሰቦች ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ እንቅፋቶች ምንድን ናቸው?** | **U.S. Citizenship and Immigration Services (የዩኤስ የዜግነት እና የስደተኛ አገልግሎቶች)**"የህዝብ ክስ" መመርያ | ይህ የፌደራል ማስታወቂያ (ከ3/13/2020 ጀምሮ) ዚጋ ያልሆኑ የ COVID-19 ምርመራ የሚያደርጉትን ከ "ህዝብ ክስ" መመርያ አንጻር ያሉትን ስጋቶች ይመለከታል። |
| | | **በ Work የህግ እርዳታ** ሰነድ የሌላቸው ሰራተኞች የስራ መብቶች ፣ የኮሮናቫይረስ አዘውትረው የሚጠየቁ ጥያቄዎች እና | የመስራት መብትን ክፍያን እና አድልዎን ጨምሮ የሚያብራሩ የመረጃ ገጾች፣ በመላው አገር ያሉ ግብአቶች ዝርዝር፣ የፋይናንስ፣ የህግ፣ የምግብ እና |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | **መልሶች በ እንግሊዘኛ , ስፓኒሽ እና ቻይኒዝ ለስደተኞች አገር አቀፍ ግብአቶች** | የህክምናን ጨምሮ |
| | | **United We Dream's ሰነድ የሌላቸው ሰዎች የጤና እንክብካቤ የማግኘት መብቶች** | ሰነድ የሌላቸውን እና/ወይም የመድን ሽፋን የሌላቸውን ታካሚዎች የሚያስተናግዱ ነጻ ወይም አነስተኛ ወጪ ያላቸው የጤና እንክብካቤ ስፍራዎች ስብስብ ። |